የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሁለተኛ አመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺ ፩ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**2nd Year No.8**
**ADDIS ABABA 8th October 2008**


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፰ /፪ሺ.ህ ፩ ዓ.ም.
"የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት
አሰጣጥ፣አስተዳደርና አመራር የወጣ ማሻሻያ
አዋጅ.............................................ገጽ ፩


**<u>CONTENT</u>**


Proclamation No 8/2008
"A Proclamation to Amend the Addis Ababa City
Government Health Service Delivery,
Administration and Management
Proclamation………………………………………………. page 1


አዋጅ ቁጥር ፰/ ፪ሺ.ህ፩ ዓ.ም.

"የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ፣አስተዳደርና አመራር ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር አመራር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፲፬/1፩/ሀ/ እና /ረ/ በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አመራር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፰/፪ሺ.ህ፩›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፰/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

PROCLAMATION No. 8/2008
A PROCALAMATION TO AMEND FOR THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT HEALTH SERVICE DELIVERY, ADNIMISTRATION AND MANAGEMENT

WHEREAS, it has become necessary to amend the proclamation in conformity with the existing conditions of the current situation for Addis Ababa city government health service delivery, Administration and Management

NOW, THERFORE, in accordance with Article 14(1)(a) and (g) of revised charter of the Addis Ababa city government proclamation No. 361/2003, the city government proclaimed this as follows.

1. Short Title

   This proclamation may be cited as the "Amended Addis Ababa city government health service, Administration and management proclamation No. 8/2008"

2. Amendment

   The Addis Ababa city government health service delivery administration and management proclamation No 108/2003 is amended as follows.


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**



ያንዱ ዋጋ 7.60
**Unit price**

፫. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ ‹‹**ከተማ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪/ ‹‹**የጤና አገልግሎት**›› ማለት የበሽታ መከላከልን፣ ቁጥጥርን፣ የተላላፊ በሽታዎች ቅኝትን፣ የአካል፣ የላብራቶሪ፣ የራጅና ሌሎች ጤና ነክ ምርመራዎችን፣ የፈውስ ሕክምናን የጤና አጠባበቅ ትምህርቶችን ማሰራጨትና የሕብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ መፈተሽና መገምገምን ያጠቃልላል፣

፫/ ‹‹**የነፃ ሕክምና**›› ማለት ወደፊት በከተማ መስተዳድሩ ካቢኔ በሚወሰነው ደንብ መሠረት ወጪው አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፣

፬/ ‹‹**ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት**›› ማለት የሕብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግ እንዲሁም በሕዝብ ጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የሕብረተሰቡ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፣

፭/ ‹‹**የጤና ተቋም**›› ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደር ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማሰራጫ ዩኒት ነው፤

፮/ ‹‹**ካቢኔ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤

፯/ ‹‹**ገቢ**›› ማለት የጤና ድርጅቶች ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች፣ የመድኃኒት ሽያጭ እና ከሌሎች አገልግሎቶች እና ዕቃዎች ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ እንዲሁም በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበሉት ዕርዳታ ነው፤

፰/ ‹‹**ሦስተኛ ወገን**›› ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን የወጪ /በኢንሹራንስ ወይንም በሌላ መልክ/ የሚሸፈን የግል ወይም የመንግስት ድርጅት ማለት ነው፤

፱/ ‹‹**የግል የጤና ድርጅት**›› ማለት በመንግሥት የሚወጡ ሕጋዊ መሥፈርቶችን በማሟላት በግል ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት የሚቋቋም የጤና ድርጅት ማለት ነው፤

፲/ ‹‹**ቢሮ**›› እና ‹‹**የቢሮ ኃላፊ**›› ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ እና የጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፤

3. Definitions

In this proclamation

1. **“City”** means the Addis Ababa City
2. **“Health Service”** means prevention and control of diseases, monitoring of contagious diseases, physical, laboratory, x-ray and other health examinations, curative treatment, the dissemination of health information and education as well as monitoring an evaluation of behavioral change in the society.
3 **.“Waiver”** means a health service delivered in free of charge whose costs are covered by appropriate public body or by other third party decided by the future regulations of the City cabinet and provided to those persons who cannot afford payment;
4. **“Exempted Services”** means health service provided in freely to all community members irrespective of level of income to improve the utilization of health services that have externalities to the general public and often reflects market failures;
5. **“Health Institution”** means hospitals, health centers, health posts, and health extension package dissemination unit, under the administration of the City Government;
6. **“Cabinet”** means the Addis Ababa City Government Cabinet;
7. **“Revenue”** means all revenue accruing to health institutions from health services they render, sales of drug another services and sales of goods as well as donations they obtain in cash or in kind;
8. **“Third Party”** means public or private organization which finances expenses of beneficiaries of medical services by insurance or other schemes;
9. **“Private Health Institution”** means a health institution established by private investors and that meets the legal requirements set by the Government.
10. **“Bureau” “Bureau Head”** means the Addis Ababa City Government Health “Bureau and Head of Health Bureau respectively;

፲፩. **‹‹የግል ሕክምና መስጫ ክፍል››** ማለት ከሆስፒታሎች የመደበኛ የሕክምና መስጫ ክፍል ውጪ የሆስፒታሉ አንድ ክፍል ሆኖ የሚቋቋም ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታከሙ የታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፣

፲፪. **‹‹የቤተሰብ ገቢ››** ማለት ቤተሰቡ ከማንኛውም እንቅስቃሴው በዓመት ወይም በወር የሚያገኘው በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ገቢ ማለት ነው፣

፲፫. **‹‹የሚገኝ ወጪን የሚሸፍን አካል››** ማለት የመክፈል አቅም ለሌላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና ወጪ በጀት ይዞ የሚሸፍን አካል ማለት ነው፣

፲፬. **‹‹የግል ሴክተር››** ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግስት መዋቅር ውጭ በግሉና በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደራጁና የሚተዳደሩትን የሚያጠቃልል ነው፣

፲፭.‹‹**ሰው**›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት **የተሰጠው አካል ነው፣**

**፲፮. የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርህ**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የጤና አገልግሎት የሚሰጡት በካቢኔው የሚወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

፪. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም፡፡

፫. በካቢኔው በሚወጣው ደንብ መሠረት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡት የነፃ የሕክምና ማስረጃ በቂ ሆኖ ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

**፬. ፈቃድ ስለማግኘት**

ማንኛውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰው ከቢሮው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

**፭. መድኃኒት**

ማንኛውም ከመድኃኒት ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማስመጣት፣ ማምረት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ እና ለታካሚዎች ማዘዝ በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፻፸፮/፲፱፻፺፩ ዓ.ም በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

11. **"Private wing"** means a unit established within the hospital operation as the general part of a hospital outside the premises reserved for regular service that renders medical service for in and out patients;
12. **"Household Income**" means the monthly or annual income earned in cash or in kind by a household from any activity.
13. "**Body Financing Costs**" means any body, which by appropriation budget, covers the medical costs of patients who cannot afford to pay;
14. **"Private**" Sector" means that health services organized and managed by private and non-governmental organization;
15. **"Person**" means a natural or juridical person

***16. Principles of Medical Service***

1. Health institutions of the City shall render medical services upon payment of the fees determined by the City Cabinet.
2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1of this Article, no person shall be denied of health services upon reason of not being able to pay.
3. A person who produces waive certificate issued by bodies authorized by the city Council shall be entitled to health services free of charge.
4. License

   No person shall provide health services without getting professional competence confirmation certificate from the bureau.
5. Drugs

   Activities related with drugs, such as importation, manufacture, distributions, sale and prescription shall only be carried out in accordance with Drug Administration and control proclamation No. 176/2001

## ክፍል ሁለት

## የጤና አገልግሎት አስተዳደር

፭. የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣን አካላት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣን አካላት፣

፩. የጤና ቢሮ

፪. የመማክርት ጉባዔ፣

፫. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፣

፬. የሆስፒታሎች አመራር፣ እና

፭. የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ናቸው፡፡

፮. የጤና ቢሮ ኃላፊ ሥልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ የጤና ቢሮ ኃላፊው የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፩/ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ሲኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር፣ የሕንፃ፣ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወስናል፣

፪/ ለግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጣል፣

፫/ የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች በሚያቀርቡት ሃሳብ መሠረት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋሞቹን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ማስገባቱን በማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነም በማሻሻል ከአስተያየት ጋር ለካቢኔው አቅርቦ ያስወስናል፣

፬/ የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች የሰው ኃይል ብቃት፣ የአሠራር ሥርዓት እና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

፭/ የጤና ድርጅቶችን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ መመሪያ ያወጣል፣ በዚህም መሠረት ለጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃ ይሰጣል፣

፮/ በከተማው ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት፣ የግብረ ሰናይና አትራፊ የሆነ የግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፣

፯/ የጤና አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ መሥፈርቶች መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፰/ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ያወጣል፣

## PART TWO

## Health Service Administration

5. ***Organs of health service administration***

Organs of the Addis Ababa City Government health service administration are:

1. Health Bureau;
2. Advisory Council;
3. Management Board of Hospitals
4. Management of Hospitals; and
5. Management of primary health care nits.

፮. ***Powers of the Head of Health Bureau***

In addition to the powers vested upon the bureau head in other provisions of this proclamation, the bureau head shall have the power to;

1/ Determine the standards for the number, qualification and composition of manpower, buildings, medical equipments and instruments for different levels of health institution;

2/ Issue license to private health institutions;

3/ upon the recommendation of health institutions and taking into consideration the cost of health institution and the ability to pay of the residents, the bureau shall propose to and get endorsement from the City cabinet the fees and charges payable for health services.

4/ assist health institutions to improve the efficiency to their manpower, develop their operational systems and institutional capacity;

5/ develop criteria to classify health institutions into different levels, apply same to classify them;

6/ Supervise health institution run by the government, charitable organizations and private profit making organizations in the City to ensure that these institutions are rendering medical service consistent with the approves standard;

7/ follow-up and control the proper implementation of various criteria, directives and regulation issued for the expansion and improvement of health service;

8/ issue directives for the implementation of this proclamation.

፲፯. የመማክርት ጉባዔ

፩/ በከተማው የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የጤና አገልግሎቱ ሽፋንና ጥራት በሚሻሻልበት የጤና ዕቅዶች ላይና በአመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ በመምከር አስተያየት የሚሰጥ የመማክርት ጉባኤ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ብዛትና ስብጥር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር ጤና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ የመማክርት ጉባዔው አካላት በቢሮው ኃላፊ ይሰየማሉ፣

፬/ የቢሮው ኃላፊ የመማክርት ጉባዔው ሥራ የሚመራበትን ሁኔታ የሚወሰን መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፰. የሆስፒታሎችና የጤና ጣቢያዎች አቋም

፩/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ሆስፒታል

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ በተደነገገው መሠረት ከሚቋቋም የሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

ለ/ የንብረት ባለቤት መሆን መከሰስና፣ በስሙ ውል መዋዋል፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል፡፡

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩-፲፫ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ቦርድ እና የሥራ አስኪያጅ ተጨማሪ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፪/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲በተደነገገው መሠረት በሚቋቋም በጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር የሚመራ ሆኖ የህግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

ለ/ የንብረት ባለቤት መሆን መክሰስና መከሰስ፣ በስሙ ውል መፈጸም፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል፡፡

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲-፲፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ አመራሩ እና የሥራ አስኪያጅ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነትና ተዛማጅ ጉዳዮች በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡



***፲፯. Advisory council***

1/ There shall be established an advisory council to assist efforts to improve the coverage and quality of health services in the City.

2/ the number and composition of members as well as powers and duties of the advisory council shall be determined by a directive issued by the bureau.

3/ Member of the advisory council shall be designated by the head of the bureau.

4/ the head of the bureau shall issue directive to determine the condition in which the advisory Council carries out its duties.

***፲፰. Hospitals and Health center personality***

1/ Every hospital under city government

a) Shall be administered by a management board having its own legal personality, in accordance with Article 10 of this proclamation.

b) has the right to own property, sue and be sued on its own name, enter into contract, operate bank account and invest its resources in development projects.

c) Notwithstanding of Article 11-13 of this proclamation, powers, functions accountability of the management Board and General Manager of the hospital shall be determined by a regulation issued by the cabinet.

2/ Every health center under the city government in Addis Ababa;

a) Shall be administered by a higher management of health center having its own legal personality, in accordance with Article 10 of this proclamation;

b) Has the right to own property, sue and be sued on its own name, enter in to contract, operate bank account and invest its resources and development projects.

c) Notwithstanding of Article 10-13 of this proclamation function responsibility, accountability and other related matters of the higher management and general manager of the health center shall be determined by a regulation issued by the cabinet.

፱. የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር መቋቋም

፩/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ

ሀ/ እያንዳንዱ ሆስፒታል በላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለጤና ቢሮው የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ በካቢኔው በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል።

ለ/ እያንዳንዱን ጤና ጣቢያ በበላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለሚገኝበት ክፍለ ከተማ የጤና ጽ/ቤት ተጠሪ የሆነ ከፍተኛ አመራር በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል።

፪/ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ እንደሁኔታው ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት አባላት ይኖሩታል እንዲሁም የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ቢያንስ ፯ ቢበዛ ፱ አባላት ይኖሩታል። የሁለቱም አሰያየም የጾታ ተዋጽኦን ባገናዘበ መልኩ ይሆናል።

፫/ የቦርድ ሰብሳቢና አባላት በከተማው ከንቲባ ይሰየማሉ፣ የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ሰብሳቢና አባላት ደግሞ በክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሰየማሉ።

፬/ የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ አባል ፀሐፊ የሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የቦርዱ አባል ይሆናል። በተመሳሳይ፣ የጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ የከፍተኛ አመራሩ ፀሐፊ፣ የጤና ጣቢያው ሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የጤና ጣቢያው ከፍተኛ አመራር አባል ይሆናል።

፭/ የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር አባላት ለማሰጡት አገልግሎት በከተማው ካቢኔ በሚወስነው መሠረት አበል ይከፈላቸዋል።

፲. የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ስልጣንና ተግባር፣

የእያንዳንዱ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድ ወይም የእያንዳንዱ የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተሉ የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን

፩/ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣

፪/ የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ እቅድ ያፀድቃል፣ የበጀት ረቂቅ መርምሮ ለቢሮው ወይም ለሚገኝበት ክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ያቀርባል፣

***9. Establishment of board of management in hospitals and higher management in health center:***

1) Under the city government

a) The board of management that administer every hospital and subordinate to Health Bureau shall be established by a regulation issued by the cabinet.

b) Higher management that administer each health center and subordinate to the sub-city health office shall be established by a regulation issued by the cabinet.

2) The board of management of the hospital shall have a minimum number of five and a maximum number of seven members and also the health center higher management shall have a minimum number of seven and a maximum number of nine members the nomination shall take into account gender balance.

3) The chair person of the board shall be designed by the mayor. The higher health management of the chairperson and the members are also designated by sub city chief executive.

4) The general manager of the hospital shall be member and secretary of the board and representatives of the staff shall be a member of the board similarly the general manager of the health center shall be the member and secretary of the higher management and representatives of the staff shall be a member of the higher management if health center.

5) Member of the management board and the higher management of the health center are entitled to be paid allowance for the service they rendered, that the amount is to be determined by the city cabinet.

***10. Powers and duties of the management board or hospitals and the higher management health center***.

Every management board of the hospital and every higher management health center based on the following sequential arrangement the hospital/the health center shall have

1) Supervise and monitor over all the activities

2) Approve the annual work plan of the hospital health center examine the budget proposed and submit it to the health bureau or to the appropriate sub city health office.

፫/ የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን ወርሃዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

፬/ የሆስፒታሉ/የጤና ጣቢያው የገቢ ምንጮች የሚተገበሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ በተግባር ላይ መዋሉንና ገቢ መደረጋቸ-ውንም ይቆጣጠራል፣

፭/ የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ የሥራ እንቅስቃሴን የሚያሻሽል የውስጥ ደንብ ያፀድቃል፣

፲፩. የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር፣

፩/ የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ የሆስፒታሉ ወይም የጤና ጣቢያ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከቦርዱ ወይም ከከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተሉ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ፣

ሀ/ የከተማውን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ለ/ የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ወይም ለከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተሉ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሐ/ የሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን የሥራ ክንውንና የሒሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ወይም ለከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተሉ ያቀርባል፣

መ/ ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን የሆስፒታላን ወይም የጤና ጣቢያው ኃላፊዎች በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሠረት አወዳድሮ በመምረጥ አቅርቦ ያፀድቃል፣

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ሆስፒታሉን ወይም የጤና ጣቢያውን ይወክላል፡፡

3) Examine and decide upon monthly, quarterly, semi-annual and annual reports of the hospital and the health center.

4) Devise the mechanisms and strategies to raise the revenue of the hospital/ health center and monitor the implementation of the same. Ensure that revenues are properly collected and timely deposited.

5) Approve internal regulation that guides the proper carrying out of the activities of the hospital or the health center.

***11. Power and duties of the general manager of the hospital and the health center.***

1) The general manager of the hospital or the health center as the chief execute of the hospital or the health center shall direct and arrange the activities of the hospital or the health center in accordance with general instruction given to him by the management board/ the higher management.

2) Without prejudice to the generality stated in sub Article of this Articles the general manager shall

a) Employ, administer and dismiss employees of the hospital in accordance with the directives approved by the city government civil service commission basic principles of the city's civil service law.

b) Prepare and submit to the management board/ the higher management the budget and work program of the hospital or the health center and implement the same upon approval.

c) Prepare and submit the higher management the operational and financial reports of the hospital or health center.

d) Select officials accountable to him based on civil service commission rules and regulations and submit to the Board or to higher management for approval.

e) Represent the hospital or the health center in all its dealing with third parties.

፫/ ዋና ስራ አስኪያጁ ለሆስፒታሉ ወይም የጤና ጣቢያው የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታሉ ወይም ለጤና ጣቢያው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፲፪. የቦርድ ወይም የከፍተኛ አመራር ተጠያቂነት

፩/ የቦርዱ ወይም የከፍተኛ አመራር ሰብሳቢ እና አባላት ከዚህ በላይ በአንቀጽ አስር /፲/ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፡፡

፪/ ሰብሳቢውና አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በሆስፒታሉ ወይም በጤና ጣቢያው ላይ ለሚደርሰው ጉዳይ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

፫/ በአብላጫ ድምጽ በሚሰጠው ውሳኔ ለሚደርሰው ጉዳት የተለየ ድምጽ ያለው አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳኋን

፲፫. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት

፩/ የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሦስት ደረጃዎች የሚከፈሉ ሲሆኑ፣

እነዚህም፡-

ሀ/ ሆስፒታል፣

ለ/ የጤና ጣቢያ እና

ሐ/ የጤና ኬላ ናቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተዘረዘሩት ደረጃዎች በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ የሚያገለግለው የሰው ኃይል መገልገያዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በቢሮው ይወሰናል፡፡

፲፬. የሙያ ሥነ ምግባር

ቢሮው የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት እና በእነዚህ የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ሊከተሉት የሚገባውን የሙያ ሥነ-ምግባር የሚመራ ደንብ አዘጋጅቶ በካቢኔው አፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፭. የሕሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓት

ሕሙማን አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ለአንድ የጤና ተቋም ወደሌላ የሚላኩበት ሥርዓት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

3) The General Manager of the hospital or health center may delegate part of this powers and duties to the officials and employees of the hospital or the health center to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the hospital or health center.

12. Accountability of the Board or the higher management

1) The Board or the chairperson of the higher management and members shall execute their duties vested in under Article 10 and above with due care.

2) The chairperson and members shall jointly and severally be liable for damages caused due to the failure to execute their duties with due care.

3) Dissenting members may not be responsible for any damage caused as a result of the decision passed by majority vote.

## ***Part Three***

## ***The Manner in which Medical Services may be provided***

13. Health delivery institutions

1) There shall be three levels of health institutions in the City. These are:

a) hospital;

b) health center, and

c) health post.

2) The Bureau shall determine qualification of manpower, standard of equipment and service provision in the health institutions under Sub article 1 of this Article.

14. Code of conduct

The Bureau shall develop code of conduct according to which public and private health institutions and medical and non-medical staff serving in such institutions must comply when performing their duties and cause same to be implemented obtaining approval from the cabinet.

15. Referral System

The referral system according to which patients may be provided proper medical care shall be determined by a directive to be issued by the bureau.

፲፮. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ስለማቋቋም

፩/ የጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ከመደበኛ አገልግሎታቸው ጎን ለጎን የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፪/ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች አሠራር፣ አመራር አስተዳደርን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል፡፡

**ክፍል አራት**

**የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች**

፲፯. ስለ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች

፩/ የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

፪/ የነፃ ሕክምና የሚሰጥበት ሥርዓት ማለትም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ማስረጃ በማን እና እንዴት እንደሚሰጥ፣ ወጪውም በማንና እንዴት እንደሚሸፈን በአዲስ አበባ ካቢኔ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፰. ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

፩/ የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ ይሰጣሉ፣

ሀ/ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ አክታ ምርመራ፣ ክትትልና የመድኃኒት አቅርቦት፣

ለ/ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

ሐ/ የቅድመ እና ድኅረ የወሊድ አገልግሎት፣

መ/ በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የማዋለድ አገልግሎት፣

ሠ/ ፀረ-ስድስት የሕፃናት በሽታዎች ክትባ፣

ረ/ ከእናት ወደ ጽንስ HIV/AIDS እንዳይተ-ላለፍ መከላከል፣

ሰ/ ሥጋ ደዌ

ሸ/ ወረርሽኝ እና

ቀ/ ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለ ክፍያ እንዲሰጡ የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣



16. Establishment of the private wings

1) Health and hospitals may establish a private wing that operated as part of the general hospital and health center.

2) The bureau shall issue a detailed directive to determine the operation and management of the private wing.

PART FOUR

Waiver Scheme and Exempted Health Service

17. Waiver Scheme

1) Citizens who can produce evidence ascertaining the fact that they cannot afford to pay for health services are entitled waiver scheme.

2) The manner is which beneficiaries are identified how and by whom should certificates of waives are to be issued and how and by whom should the cost be reimbursed to facilities shall be determined by the regulations to be issued by city government cabinet.

18. Exempted Health Services

1)The City Government health service delivery institutions may render health service in free of charge in the following categories.

a) Diagnosis, following up and supply of medical treatments for tuberculosis.
b) Family planning services.
c) Pre and post natal services:
d) Delivery service in basic health service institutions;
e) Expanded programmed of immunization for children under five.
f) Prevention of HIV/AIDS transfer from mother to child.
g) Leprosy
h) Epidemic and
i) Other health services to be provided free of charge on reason of future decision.

፪/ ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ የጤና ተቋም በዚህ ዓይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሳይ መረጃ ለይቶ በመያዝ ለቢሮው ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ፋይናንስ

**፲፱. የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የፋይናንስ ምንጭ**

/ በከተማው አስተዳደር በጥቅል የሚመደብ በጀት፣

2/ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ እና

3/ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ከሚቀበለው ዕርዳታ ይሆናል፡፡

**፳. በገቢ ስለመጠቀም**

፩/ ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የሚያገኙት ገቢ በጤና ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡

፪/ ማናቸውም የአስተዳደሩ ሆስፒታል/ጤና ጣቢያ የሚያገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ የበጀቱ አካል ሆኖ፣ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ የበጀት አዋጅ በሚፈቀደው መሠረት ለሥራው ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

፫/ የሆስፒታሎች/የጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ኦዲት ይደረጋል፡፡

፬/ የሆስፒታሎች/የጤና ጣቢያዎች የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዝርዝር አፈጻጸም የሚያሳይ መመሪያ ቢሮው ከፋይናንስ ቢሮው ጋር በቅንጅት ያወጣል፡፡

**፳፩. የጤና አገልግሎት ክፍያ**

፩/ ለከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት ሊፈፀም የሚገባው ክፍያ ልክ በካቢኔው እየተወሰነ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪/ የጤና ቢሮው የጤና አገልግሎት ክፍያ ልክን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንዲከናወን በማድረግ የውሣኔ ሃሣብ ለከተማው ካቢኔ ያቀርባል፡፡

፫/ የጤና ቢሮው ከሆስፒታሎች ወይም ከክፍለ ከተማው ጤና ዴስክ ከአስተያየት ጋር የሚቀርብለትን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለከተማው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

2) Health institution that provides exempted health services shall keep adequate record and report same to the Head of the Bureau.

## PART FIVE
## Finance of Hospitals/Health Centers under the City Government

***19. Sources of Fiance of hospitals/Health Centers***

1) Block budget appropriated by the Addis Ababa City Government;

2) Revenue from medical services the hospital/health center provide and

3) Aid in cash and in kind obtained by the hospital/health center from domestic sources and sources outside the country.

***20. Revenue utilization***

1) Revenue obtained by hospitals/health centers shall be deposited in a special bank account opened in name of the hospital/health center.

2) In addition to the block budget appropriated to them by the city cabinet. Each and every hospitals health centers and authorized to use all revenue they obtain from service they provided.

3) The collection and utilization of revenue obtained by hospitals/health centers shall be audited by a body authorized by the government.

4) A directive for the detailed performance of the collection and utilization of revenue obained by the hospitals/health centers shall be issued by the bureau in consultation with finance bureau.

***21. Health Service fees***

1) The City cabinet shall determine fees payable for health services provided by health institutions under the Addis Ababa City Government.

2) The health bureau management shall cause, as necessary, study for the revision of fees and submit its proposal to the City cabinet as the case may be.

3) The Bureau shall, togethe with its recommendations, submit to and get approval from the City Council on the proposals it receives from the hospitals or sub-city health desks.

፲፩

**፳፪. የዕቃና አገልግሎት ግዢ**

፩/ ጤና ተቋሞች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት የከተማው አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡

፪/ ማናቸውም የአስተዳደሩ ሆስፒታል/ጤና ጣቢያ በእራሱ ሀብት፣ አመራር አስተዳደር ለሆስፒታሉ/ለጤና ጣቢያው ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችል ማናቸውም ህጋዊ ባለሀብት ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በውል መስጠት ይችላል፡፡

፫/ ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በውል በሦስተኛ ወገን የሚሰጡበት ሁኔታ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፫. የጤና መድን ዋስትና

፩/ የከተማው አስተዳደር የጤና መድን ዋስትና ለማቋቋምና ለማስፋፋት የሚረዱ ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

፪/ የጤና መድን ዋስትና የሚከተሉትን የአደረጃጀት ዓይነቶች መሠረት በማድረግ ይቋቋማል፣

ሀ/ የግል ድርጅቶች በሚያቋቁሙት የጤና መድን ዋስትና ፖሊሲ፣

ለ/ የተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማት የጤና መድን ሥርዓት እንዲዘረጉ በማድረግ፣

ሐ/ አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና መድን ፖሊሲዎችን በመግዛት ወይም በራሳቸው የመድን ሽፋን እንዲያቋቁሙ በማድረግ፣

መ/ መንግሥት ለሠራተኞች ማኅበራዊ የጤና መድን በማቋቋም፡፡

## ክፍል ስድስት
## የማሕበረሰብ ተሳትፎ

**፳፬. የተሳትፎው ዓላማ**

የማኅበረሰብ ተሳትፎ ዋነኛ ዓላማ ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የመከላከል አገልግሎቶችን ለማጠናከርና በጤና ተቋሞች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ይሆናል፡፡

**፳፭. በዕቅድ ዝግጅት መሳተፍ**

የመከላከል ፕሮግራም ነዳፊዎችና የጤና ተቋሞች በዕቅድ ዝግጅት ሂደት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ አመቺ በሆነ መንገድ የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች አስተያየት ማግኘት አለባቸው፡፡



**22. Procurement of goods and services**



1) Hospitals shall procure goods and services in accordance with the Government procurement Directives.
2) Each and every hospital or health center may outsource non-clinical services by contract to private and other institution that can provide efficient services to the hospital with their own resource and management.
3) The condition in which non-clinical services may be outsourced to third parties shall be determined by the directives to be issued by the bureau.

***23. Health Insurance***

The City Government shall create conducive environment for the expansion and establishement of health insurance schemes

1) The health insurance scheme may be established based on the following types of organization,
   a) Private health insurance policy;
   b) by encouraging communities to establish their own health insurance scheme;
   c) by encouraging employers to established their own health insurance schemes or to buy insurance policies;
   d) by establishing social health insurance schemes to civil servants.

## PART SIX
## Community Participation

24. Objective of participation

The main objectives of community participation are to strengthen the preventive and promotive care and to raise the quality of health services of health institution.

2.5. Participation in planning

Preventive health functionaries and health functionaries and health institutions may whenever possible get the views of the beneficiaries in the process of preparation of plans as well as during evaluation of implementation of such plans.



***ክፍል ሰባት***

**<u>*የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ ትብብርና አስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት*</u>**

***፳፮. የሥራ ከባቢን ስለማሻሻል***

*፩/ ቢሮው የግሉ ዘርፍ በጤናው ሴክተር የበለጠ ተሳታፊ የሚያደርገውን ወሳኝ የማትጊያ ስልቶች በመለየት ሃሣብ ያቀርባል፣ በተጨማሪም የአቻ ተጽዕኖን በመጠቀም የተሻለ ከባቢ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡*

*፪/ ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን በማስፈን ረገድ ከግሉ ዘርፍ ጋር በቅንጅት የሚሠራበትን ስልት ይነድፋል፡፡*

***፳፯. የምክክር መድረክ***

*ቢሮው ከግሉ ዘርፍ ጋር በፖሊሲ፣ በቴክኒካዊ፣ በአሠራርና በቅንጅት ላይ ለመምከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የምክክር ጉባኤዎች ያካሂዳል፡፡*

***፳፰. ድጋፍ ስለማድረግ***

*፩/ ቢሮው የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት እንዲስፋፉ እና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል የቴክኒክ ዕገዛ ያደርጋል፡፡*

*፪/ ቢሮው በመንግሥት የሚደረጉ የሥልጠናና የአሠራር መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡*

***፳፱. መረጃን ስለማጠናከር***

*፩/ የግሉ ዘርፍ የሚያደርገውን ተሳትፎና የሚያጋጥመውን ችግር በአግባቡ ማወቅና እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ቢሮው በግሉ ዘርፍ ላይ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ጥናቶችንም በቋሚነት ያካሂዳል፡፡*

*፪/ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፡፡*

*፴/ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት*

*፩/ ቢሮው በአገር አቀፍና በተለይም በከተማው ውስጥ በወረርሽኝ መልክ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን በመለየት ተገቢውን መረጃ ወቅታዊና ቀጣይ በሆነ መልኩ ያሰባስባል ያሠራጫል፡፡*

*፪/ ቢሮው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂስትክስ አቅም እንዲገነቡ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብዓቶችን እንዲመቻቹ ያደርጋል፡፡*

**<u>PART SEVEN</u>**

***<u>Public, Private Sector Cooperation and Emergency Health Service</u>***

***26. Improving the working environment***

1) The bureau shall identify and propose revisions on key incentives in addition use peer pressure among the private sector participants to promote their increased and active participation.

2) The bureau shall develop a strategey to work together with the private sector to ensure that health services are conducted in proper code of conducts.

**27. Consulation forum**

The bureau shall, at least twice a year, conduct a consulative forum with private sector on policy, technical, systemic and coordination issues.

**28. Support**

1) The bureau shall give the necessary technical assistance to private health institution with the objectives of enabling them to expand and improve quality of services.

2) The bureau shall cause the participation of private sector in government sponsored relevant trainings and development of guidelines.

**29. Strengthening of information base**

1) The bureau shall collect information on regular basis and undertake studies on the participation and constraints of the sector to know and take actions to foster its participation.

2) Public and private health institutions shall exchange information concerning type and spread of diseases in accordance with the directive to be issued by the Bureau.

***30. Emergency Health Service***

1) The bureau shall timely collect, analyze and distribute information on diseases that are likely to turn to epidemic proportions nationally and particularly in the City.

2) The bureau shall build the information, logistic capacity of health manager and institutions as well as prepare contingency stock of inputs to prevent epidemic and to respond as immediately as possible.

፫/ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የሚደርሰውን የሕዝብ ጤናና ሕይወት አደጋ ለመቀነስ እንዲቻል ቢሮው የሁሉን ተሳትፎና አስተዋጽኦ በተለይም የኅብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎና በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቢሮው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፴፪. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፫. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

መስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ



3) The bureau shall organize and implement the delivery of emergency, health services with the full participaion of communities in general and all stake holders in particular to reduce death and human suffering; monitor the implementation of same.

## PART EIGHT
## Miscellaneous Provisions

31. Power to issue Regulations and directives

1) The Cabinet shall issue regulations for the proper implementation of this proclamation.

2) The Bureau shall issue detailed directive that will facilitate the implementation of this proclamation

32. Inapplicable Laws

Any proclamation, regulation, directive or practices, which are inconsisten with this proclamation, shall have no application with respect to matters provided for in this proclamation.

33. Effective Data

This proclamation shall come into force on 8th day of October 2008 G.C

Addis Ababa

Done at this 8th day of October 2008

Kuma Demeksa

Mayor of Addis Ababa City